# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።




ሊቃነ ጳጳሳቱ በበይነ መረብ በነበረው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐግብር

በአውሮፓ የአራቱ ሐገረ ስብከቶች የጋራ ግብረ ኃይል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐግብር አከናወነ ዓርብ መጋቢት ሃያ ዘጠኝ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሌሊቱ ሰባት ድረስ መርዳት ቅን ልብን እንጂ ባለ ጸግነትን አይጠይቅም በሚል መነሻ እርስ በሃይማኖታቸውና በማንነታቸው ምክንያ ቤት ንብረት ላጡ እንዲሁም አሳዳጊዎች የሞቱባቸው እጓለ ማውታ ለሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞች አጋርነታቸውን ለማሳየት ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የስዊድንና ስካንዲብያን ሐገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ የጣሊያንና አካባቢው ሐገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በተገኙበት የእርዳታ መርሐ ግብር የተካሄደ ሲሆን በነበርው የገንዘብ ማሰባሰብ መርሐግብር መምሕር ብርሃኑ አድማስ ከኢትዮጵያና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው አንግዶች መምህራን እና ዘማርያን በየጾጋቸው አገልግሎት በመስጠት ተሳተፈዋል።ወደ መቶ ሃያ አራት የሚደርሱ ቀን ክርስቲያኖች የተሳተፉ ሲሆን በማግስቱ ጨምሮ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ኢሮ ተለግሶኣል

በመሆኑም በዕለቱ በነጋታውም ቀጥሎ የተሰበሰበው የንዘብ መጠን

በጎፈንድ ሚ 3845 €

በጀርመን ሐገር ስብከት የበጎ አድራጎት አካውንት 2314€

በስዊድን ሐገረ ስብከት ዝክረ ነዳያን የበጎ አድራጎት ማሕበር 1500€

በፈረንሳይ የልዮን ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ምዕመናን 1610 € የለገሱ ሲሆን በአጠቃላይ በእለቱ የተሰበሰበው ገንዘብ 9,269€ ሲሆን በኢትዮጵያ ወደ አንድ ሚልየን 19 ሺ የኢትዮጵያ ብር ይገመታል። ይህንን ገንዘብ ዝክረ ነዳያን ዘ አበዊነ ሐዋርያት የዲያስፖራ አካውንት በአዲስ አበባ አሀዱ ባንክ በሚል የበጎ አድራጎት አካውንት ገብቶ በብፁዕ አቡነ ኤልያስ የስዊድንና ስካንዲብያን ሐገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ኃላፊነት ለተጎጅዎች እንዲደርስ በአውሮፓ የአራቱ ሐገረ ስብከቶች የጋራ ግብረ ኃል ፳፭ ሚያዚያ ፳፻፲፭/ 03 May 2023 በነበረው መደበኛ ስብሰባው ወስኗል።